# <u>ይድረስ ለክቡር አቶ ወንድሙ ኢብሣ</u>
# “ለመስራት ያልታደለ አእምሮ ለማፍረስ ተወዳዳሪ የለውም”

**(ከአብዱራህማን አህመዲን - በግል)**

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን በመወከል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ አቶ ወንድሙ ኢብሣ በጎግል ጋዜጣ ቅጽ 3፣ ቁጥር 077፣ በመጋቢት 18 ቀን 2001 ዓ.ም እትም፣ በገጽ 3 ላይ፤ “ትዝብት፣ ትንግርትና አግራሞት በኢፌዲሪ 3ኛ ዓመት ፓርላማ - 2001” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጽሑፍ ነው።

መጣጥፉ ሥነ-ጽሑፋዊ ደረጃውን ያልጠበቀ፣ ቅደም ተከተላዊ የሃሳብ ፍሰት የሌለው፣ በቃላት ኳኳታ የተሞላ የአሉባልታ ቱማታ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። በርግጥ ጸሐፊው ከዚህ የተሻለ ቁም ነገርን እንዲያፈልቁ መጠበቅ “ከእባብ እንቁላል እርግብ” መመኘት ይሆናል። ለአንዳንዶች፣ በኢዴፓ ላይ “አሉባልታ መንዛት” የተለመደ “የትግል ስልት” በመሆኑ፤ ይህንን የአቶ ወንድሙን ጽሑፍ አይተን እንዳላየን በመሆን በሳቅ፣ በፈገግታና በአርምሞ ማለፍ ይቻል ነበር። ይሁን እንጂ፣ በአንድ በኩል ለጋዜጣው አንባቢዎች ሀቁን ለማስጨበጥ፤ በሌላ በኩል ብዕር የጨበጠና “መጻፍ የቻለ” ሁሉ መሰረት የሌለው አሉባልታ በማሰራጨት ጊዜና ወረቀት ከማባከን አልፎ ሕዝብን ማደናገር የማይችል መሆኑን ተገንዝቦ ከኢዴፓ ላይ እጁን እንዲሰበስብ የማያዳግም ትምህርት መስጠቱ አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ጸሑፍ ለማዘጋጀት ተገድጃለሁ።

“በፓርላማችን የፖለቲካ አሰራር ውስጥ በየጊዜው ብታዘብም ይሉኝታ ባጣ መልኩ እንደ መጋቢት 10 ቀን 2001 የጥያቄና መልስ ውሎ ተገርሜ፣ ተደንቄ፣ ተሸማቅቄ አላውቅም…” ይላሉ የተከበሩ አቶ ወንድሙ ጽሑፋቸውን ሲጀምሩ። ጸሐፊውን እንዲህ “ያስገረማቸው” እና “ያሸማቀቃቸው” ጉዳይ ምንድነው? የሚል ጥያቄ አንስተን መልሱን ለማግኘት ወደ ጽሑፋቸው ቀጣይ ክፍል ስናመራ ደግሞ፤ “ቀኑ የጥያቄና መልስ ቀን ነው… ጥያቄዎቹም… የምክር ቤት አባላት ተብለው ግን የአንድ ፓርቲ አባሎች ብቻ… እንዲስተናገዱ…” መደረጉ ለመገረማቸውም ሆነ ለመሸማቀቃቸው ምክንያት እንደሆነ ያስረዱናል፣ ክቡር አቶ ወንድሙ።

የተከበሩ አቶ ወንድሙ እንዳሉት በዕለቱ ከቀረቡት አስር ጥያቄዎች ውስጥ ሰባቱ በኢዴፓ፣ ሁለቱ በኢህአዴግ እና አንዱ ደግሞ በቅንጅት አባላት ነበር የቀረቡት። እነዚህ የምክር ቤት አባላት ጥያቄ ማቅረባቸው አቶ ወንድሙን ለምን እንዳስገረማቸው ባይገባኝም፤ ፓርቲያቸው (ኅብረት) “አንደኛ ተቀዋሚ ፓርቲ” ሆኖ ሳለ በዕለቱ አንድም ጥያቄ ሳያቀርብ ሌሎች ፓርቲዎች ጥያቄ በማቅረብ የምክር ቤቱን መድረክ መቆጣጠራቸው በርግጥም “ሊያሸማቅቃቸው” እንደሚገባ ግን እገነዘባለሁ።

በእለቱ የኢዴፓ አባላት ሰባት ጥያቄ ማቅረብ የቻሉት ግን አቶ ወንድሙ በጽሑፋቸው ላይ እንደጠቀሱት ከኢህአዴግ ጋር በመሞዳሞድና “ድራማ” በመስራት ሳይሆን፤ የምክር ቤቱ ደንብ የሚፈቅደውን መብታቸውን አሟጠው በመጠቀማቸው ያገኙት ውጤት ነው። ይህ ሁኔታ በቀጣይ የምክር ቤቱ ዘመንም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን “ወዳጅም፣ ጠላትም” ቢያውቀው መልካም ነው። እዚህ ላይ እነ አቶ ወንድሙ ይህንን የጥያቄና መልስ መብታቸውን ለምን አልተጠቀሙም? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። አቶ ወንድሙ በጽሑፋቸው ላይ እንዳሉት “ለሀገር የሚጠቅሙ ጥያቄዎቻቸው ውድቅ ተደርገውባቸው” እንዳልሆነ ግን አጣርቻለሁ። እናስ ችግሩ ምንድነው?

እነ አቶ ወንድሙ ጥያቄ የማያቀርቡት ፓርቲያቸው በሚከተለው “ተራ የፖለቲካ ጨዋታ” ምክንያት እንደሆነ የአቶ ወንድሙ ፓርቲ መሪዎች እንጂ፣ አቶ ወንድሙ ራሳቸው የሚያውቁት አይመስለኝም። ነገሩን ለመረዳት ግን ብዙ መመራመር የሚያስፈልገው አይደለም። ይኸውም፤ ፓርቲያቸው “በሀገሪቱ ያለው የፖለቲካ ምህዳር ጠቧል” የሚል አቋም እያራመደ ስለሆነ፣ እነ አቶ ወንድሙ የምክር ቤቱ ደንብ በሚፈቅደው መሰረት ጥያቄ እያቀረቡ ተሳትፎ ቢያደርጉ ፓርቲያቸው “ጠቧል” እያለ የሚያራምደው አቋም ተቀባይነት ያጣል። እናም፣ እነ አቶ ወንድሙ ፓርቲያቸው የፖለቲካ ኪሳራ እንዳይደርስበት “ጥያቄ ባለማቅረብ” ሌላ የፖለቲካ ኪሳራ መክሰርን መረጡ። እኛ የተገነዘብነው ይህንን ነው። ከዚህ አኳያ ነው እኛና እነ አቶ ወንድሙ የምንከተለው የትግል ስትራቴጂም ሆነ ስልት ለየቅል የሆነው። ኢዴፓ እንዲህ ያለውን “የፖለቲካ ቲያትር” ለመተወን የሚያባክነው ጊዜ አይኖርም። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ከተራ ድርጅታዊ ጥቅም ይልቅ ለሕዝብ ጥያቄዎች ቅድሚያ የምንሰጥ በመሆኑ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀምን የፖለቲካ ምህዳሩ የበለጠ እንዲሰፋ እንታገላለን።

ወደ ሌላ ጉዳይ እናምራ። ለክቡር አቶ ወንድሙ አንድ ሌላ ጥያቄ ላቅርብ። ክቡር ሆይ! እናንተ በራሳችሁ ምክንያት ጥያቄ ባለማቅረባችሁ የኢዴፓ አባላት ሊወቀሱ ይገባል ወይ? “የዋናው ተቃዋሚ” ፓርቲ አባላት ጥያቄ ሳያቀርቡ ሌሎቹ ፓርቲዎች መጠየቅ አይችሉም የሚልስ ሕግ አለ ወይ?

ሌሎች ፓርቲዎችና አባላቶቻቸው ያልሰሩትን ሥራ ኢዴፓና አባላቱ በመስራታቸው “ተጋለጥን” የሚል ስጋት እየፈጠረባቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ኢዴፓን ሲወቅሱና ሲከሱ፤ አለፍ ሲልም የአሉባልታ እሩምታ በማውረድ ኢዴፓ “በሕዝብ እንዲጠላ” እንቅልፍ አጥተው እንደሚያድሩ ለዓመታት ስንታዘብ ኖረናል። በሀገሪቱ “አሉ” የተባሉ “የፖለቲካ ጎምቱዎች” ጭምር ከዕድሜአቸው፣ ከዕውቀታቸው፣ ከልምዳቸው፣ ከክብርና ዝናቸው የማይመጣጠን አሸሙርና አግቦ በጋዜጦች ላይ ሲያሰራጩ በዝምታ ስንከታተል ባጅተናል። እንዲህ ያለውን ሁኔታ “ለመስራት ያልታደለ አእምሮ ለማፍረስ ተወዳዳሪ የለውም” ብሎ ከማለፍ ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል? በኔ እምነት፣ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ከዴሞክራሲ አስተሳሰብ ማዕቀፍ ውጭ በመሆኑ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እታገላለሁ ከሚል አካል ሁሉ የማይጠበቅ ነው።

በክቡር አቶ ወንድሙ ጽሑፍ ውስጥ ያየሁት ሌላው መልስ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ፤ የኢዴፓ አባላት "መንግስት መልስ ሊሰጥባቸው ይገባል" ያሏቸውን ጥያቄዎች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በማቅረባቸው፤ ከገዢው ፓርቲ "ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው ተለጣፊዎች" እንደሆኑ ለማስመሰል የሄዱበት ጠመዝማዛ መንገድ ነው። አቶ ወንድሙ እንዲህ ከሚናውዙና በገደምዳሜ ከሚናገሩ (ማስረጃ ካላቸው) "ኢዴፓና አባላቱ የኢህአዴግ ተለጣፊ ናቸው" ብለው በግልጽ ቢናገሩ ቢያንስ ቢያንስ ከድካም ይድኑ ነበር።

እንዲህ ዓይነቱ ከአርባ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ የፍረጃ ፖለቲካ፤ የሀገሪቱ ፖለቲካ አለማደጉን ከማሳየት የዘለለ ትርጉም የለውም። አሉባልታና ፍረጃ አንድን ፓርቲ ያፈርስ ቢሆን ኖሮ፤ ኢዴፓ መፍረስ የነበረበት በተመሰረተ ማግስት ነበር። የኢዴፓን አስተሳሰብ "ማሸነፍ" ያቃታቸው ሁሉ ይህንን ቀላልና ተራ የትግል ስልት ሲከተሉ ይስተዋላል። እንግዲህ አቶ ወንድሙም ይህንኑ አቋራጭ "ኢዴፓን የማጥፋት" መንገድ መከተላቸው ነው። ይህ ስልት ሌሎችን እንዳላዋጣ ተረድተው ስልታቸውን ቢቀይሩ እንኳ ምናለ? እንደ በግ አንዱ በሄደበት የመከተል (ፈረንጆቹ Sheep Mentality የሚሉት) አባዜስ የሚቆመው መቼ ይሆን?

እዚህ ላይ ግን ለክቡር አቶ ወንድሙ አንድ ተጨማሪ ጥያቄ ለማንሳት እወዳለሁ። ይኸውም፣ ባለፉት ዓመታት አቶ ወንድሙና ሌሎች "ጓዶቻቸው" ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሌሎች ሚኒስትሮች ጥያቄዎችን ያቀርቡ ነበር። ታዲያ እናንተ እነዚያን ጥያቄዎች ማቅረብ የቻላችሁት (እናንተም ሆናችሁ ፓርቲያችሁ) የኢህአዴግ ተለጣፊዎች በመሆናችሁ ወይም ከመጋረጃው በስተጀርባ ከኢህአዴግ ጋር ተደራድራችሁ ድራማ ብጤ በመስራት ነበር እንዴ? መልሱን ለህሊና ፍርድ እተወዋለሁ። እንዲያው ለነገሩ፣ በዓላማም ይሁን በአደረጃጀት ወይም በአሰራር ከኢህአዴግ ጋር የሚመሳሰለው ማን ነው? እናንተ ወይስ ኢዴፓ?

ጽሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት እወዳለሁ። በመሰረቱ የአንድ ፓርቲ አባል በሌላው ፓርቲ የሚከናወኑ ህፀፆችን ነቅሶ በማውጣት፣ በማስረጃ አስደግፎ መተቸት ወይም ማጋለጥ ወይም ማብጠልጠል ያለ፣ የነበረና ወደፊትም ሊኖር የሚገባው አሰራር ነው። የተከበሩ አቶ ወንድሙ ያቀረቡት ጽሑፍ ግን ፍሬ የሌለው የአሉባልታ ስንክሳር ከመሆኑም በላይ "የራስን ድክመት" ለመሸፈን የተደረገ ግብግብ ስለሆነ በእኔ በኩል "ገንቢ ነው" የሚል እምነት የለኝም።

ክቡር አቶ ወንድሙ፤ የኢዴፓ አባላት ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በየመሸታ ቤቱ አምባጓሮ በመጫር ወይም በሌላ በማይመጥናቸው አልባሌ ስፍራ በመገኘት ሳይሆን፣ የመረጣቸው ሕዝብ የሰጣቸውን ሀላፊነት እንዴት መወጣት እንደሚገባቸው በመመካከር መሆኑን በአጽንዖት ሊረዱት ይገባል። ስለሆነም፤ እናንተ ወደዳችሁትም ጠላችሁት፣ በየጋዜጣው ላይ ጻፋችሁም አልጻፋችሁ፣ እናንተ ጥያቄ አቀረባችሁም አላቀረባችሁ፣ የኢዴፓ አባላት "ሕዝብ ሊያውቀው ይገባል" ብለው ያመኑበትን ጥያቄ ከመጠየቅ አይቆጠቡም።

ከዚህ በተረፈ፣ እኔ አቶ ወንድሙ "የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል" የሚለውን አቋማቸውን ለማረጋገጥ እየሄዱበት ያለውን የተሳሳተ አቅጣጫ በመተው በቀሪው የምክር ቤት ዘመን የተሻለ ስራ በመስራት "ከመሸማቀቅ" መዳን የሚችሉ መሆኑን እመክራለሁ።